የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ. ሳ.ቁ 1367፥ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: ሐምሌ 2 2 2014
ቁጥር/REF NO: 01/12.47/231/14

ለሁሉም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት
**ባሉበት**

ጉዳዩ፡- **የከፍተኛ ትምህርት ስኮላርሽፕ ማስፈፀሚያ መመሪያን ይመለከታል፤**

ትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀፅ 86 (5) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ሃገራዊ ዝቅተኛ የትምህርት ብቃት መመዘኛዎችን፣የሙያ ስነምግባር ደንቦችን እና ተቋማት ሊከተሏቸው የሚገቡ የአሰራር ስነ ስርዓትን እንደሚያወጣ ይደነግጋል፡፡

በዚሁ መሠረት ለከፍተኛ ትምህርት የስኮላርሽፕ አሰጣጥ ሥርዓት ለመዘርጋትና ሂደቱን በብቃትና በጥራት ለማስተዳደር የከፍተኛ ትምህርት ስኮላርሽፕ ማስፈፀሚያ መመሪያ ተዘጋጅቶና በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ መመሪያ ቁጥር 916/2014 ሆኖ የፀደቀ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

**ግልባጭ**፡-

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
- ለአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈጻሚ
  **ትምህርት ሚኒስቴር**

# የከፍተኛ ትምህርት ስኮላርሽፕ ማስፈጸሚያ

## መመሪያ ቁጥር 916 /2014

ትምህርት ሚኒስቴር

ሐምሌ / 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መቅድም

በሀገራችን ለትምህርት ጥራት ልዩ ትኩረት የተሰጠ መሆኑና የመምህራን ትምህርት ደረጃና ብቃት ቁልፍ በመሆኑ ለዘላቂና ሁለንተናዊ ልማት መረጋገጥ አስተዋጽዖ ማድረግ ይቻል ዘንድ የከፍተኛ ትምህርት የስኮላርሽፕ አሰጣጥን በሥርዓት በመምራት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን፣ ተመራማሪዎችና ሰልጣኞችን አቅም መገንባት በመንግስት በጽኑ የሚታመን በመሆኑ፤

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ዕድል አሰጣጥን ውጤታማ ለማድረግ ወጥ፤ ግልፅና ፍትሃዊ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ሌሎች ተቋማት ብቁና በቂ የሰው ሀይልን ለማፍራት አማራጭ ስኮላርሽፕ ፕሮግራሞችን በማበረታታት የመንግስትን በጀት እና ወጪ መቀነስ በማስፈለጉ፤

በመንግስት ዩኒቨርስቲዎች እና ሌሎች ተቋማት የተናበበ ሥርዓት በመዘርጋት፣ በመምራትና በማስተዳደር ውጤታማ የሆነ የከፍተኛ ትምህርት የስኮላርሽፕ አሰጣጥን ለመተግበር በሁሉም ደረጃ ተዓማኒነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ሥርዓት እንዲኖር በማስፈለጉ፣

የትምህርት ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 86 (5) በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት ተቋማት የተሟላ ነፃነት እስኪጎናፀፉ ድረስ ይህንን ለመንግስትና ለግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚ ሰራተኞች፣ ለሌሎች ተቋማት ሰራተኞች እና ለበትረ ሳይንስ ተማሪዎች የሚሰጥ የስኮላርሽፕ ማስፈጸሚያ መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የከፍተኛ ትምህርት የስኮላርሽፕ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 916/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 2 አውጪው ባለሥልጣን

የትምህርት ሚኒስቴር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 86 (5) በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት ይህንን የከፍተኛ ትምህርት የስኮላርሽፕ ማስፈጸሚያ መመሪያ አውጥቷል፡፡

## አንቀፅ 3 ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት በአዋጅ 1152/2011 ትርጉም ይይዛሉ፡፡

1/ **"ሌሎች ተቋማት ማለት"** በጀቱ በፌዴራል ወይም በክልል መንግስት የሚመደብለት ሆኖ ተጠሪነቱ በየደረጃው ላሉ የመንግስት መዋቅር ውስጥ ህግ አውጪ፣ ህግ ተርጓሚና ህግ አስፈጻሚ ተቋም ማለት ነው፤

2/ **"በትረ ሳይንስ ፕሮግራም ማለት"** በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ እና በኢንጂነሪንግ የሙያ መስኮች በልዩ ሁኔታ በውጭ ሀገራት ዩኒቨርሲቲዎች በረጅም እና አጭር ጊዜ ትምህርትና ሥልጠና በውጭ ሀገራት ሳይንስና ቴክኖሎጂን ላይ ትኩረት በማድረግ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን እና ተሞክሮዎችን ወደ አገር ቤት ለማስፋት ታስቦ የተዘጋጀ ልዩ የስኮላርሽፕ ፕሮግራም ነው፡፡

3/ **"ስኮላርሽፕ"** ማለት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ የሚሰጥ የትምህርትና ሥልጠና ዕድል ነው፡፡

4/ **"የአጭር ጊዜ ሥልጠና"** ማለት ሰልጣኙ ካለው ሙያ ጋር ተዛማጅ የሆነ ለተቋሙ ተልዕኮዎች መሳካት የሚያግዝ ከሶስት ወራት ያልበለጠ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ማለት ነው፡፡



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

5/ **“የረጅም ጊዜ ትምህርትና ሥልጠና”** ማለት ሰልጣኙ ካለው ሙያ ጋር ተዛማጅ የሆነ እና የትምህርት ደረጃ ሊያሳድግ የሚያስችል እና ለተቋሙ ተልዕኮዎች መሳካት የሚያግዝ ሥልጠና ማለት ነው፡፡

6/ **“ሠልጣኝ”** ማለት በመጀመሪያ ዲግሪ፤ በሁለተኛ እና በሦስተኛ ዲግሪ፣ በህክምና ትምህርት መስክ በስፔሻሊቲ፣ በድህረ ስፔሻሊቲ፣ በድህረ ዶክቶራል ዲግሪ እንዲሁም ሌሎች አጫጭር ሥልጠናዎች ዕድል የተሰጠው ሰራተኛ ማለት ነው፡፡

7/ **“አገልግሎት”** ማለት ተወዳዳሪው ባለው የትምህርት ዝግጅት/ሙያ ተሰማርቶ የተገኘ የስራ ልምድ ነው፡፡

8/ **“የትምህርትና ሥልጠና አበል”** ማለት ሰልጣኙ በትምህርትና ሥልጠና ላይ ለሚቆይባቸው ጊዜያት እንዲከፈል የተፈቀደ የመኖሪያ፣ የምርምር፣ የጤና ኢንሹራንስ እና ለሌሎች ወጪዎች የሚውል የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡

9/ **“በመንግስት የተገኘ ስኮላርሽፕ”** መንግስት ከሌሎች ሀገራት መንግስታት ጋር ስምምነት እና መንግስት ከልማት አጋሮች ጋር በሚያደርገው ስምምነት የሚገኝ የአጭርና የረጅም ጊዜ የትምህርትና ሥልጠና ዕድል ማለት ነው፡፡

10/ **“በግል የተገኘ ስኮላርሽፕ”** ማለት አንድ የከፍተኛ ትምህርት ሰራተኛ ወይም የሌላ ተቋም ሰራተኛ በግሉ በመጻጻፍ ያገኘው የአጭር/ረዥም ጊዜ የትምህርትና ሥልጠና ዕድል ማለት ነው፡፡

11/ **“ጆርናል”** ማለት በዩኒቨርሲቲዎች ወይም በምርምር ተቋማት ደረጃ የአካዳሚክና አካዳሚክ ነክ የሆኑ የጥናትና የምርምር ጽሁፎችን የሚያወጣ ደረጃው የተመሰከረለት ህትመት ነው፡፡

12/ **“ፕሮሲዲንግ”** ማለት በዩኒቨርሲቲዎችና በምርምር ተቋማት ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ተቋማት ደረጃ በዐውደ ጥናቶች ላይ የቀረቡ የጥናትና ምርምር ፅሁፎች የሚታተሙበት መድብል ነው፡፡

13/ **“የሥራ ክፍል”** ማለት በመንግስት መስሪያ ቤቶች በተለያዩ የስራ መዋቅሮች ያለ የሲቪል ሰርቪስ አደረጃጀት አንድ ክፍል ማለት ነው፡፡

14/ **“ሚኒስቴር”** ወይም **“ሚኒስትር”** ማለት በቅደም ተከተል የትምህርት ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ማለት ነው፡፡

15/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

### አንቀፅ 4 የመመሪያው አስፈላጊነት

ሀገራችን ቅድሚያ ትኩረት ሰጥታ በለየቻቸው መስኮችና አሁን በመሰራት ላይ ያለውን የሰው ኃይል አቅም ግንባታ ትኩረት ባደረገ መልኩ ለማስኬድ የሚሰጡ የአጭርና የረጅም ጊዜ የትምህርትና ሥልጠና ዕድሎችን ጥራትና ብቃት ለማረጋገጥ፣ በምልመላና በትግበራ ሂደት ግልጽና ፍትሀዊ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ አሰልጣኝ ተቋማት ለየትምህርት ፕሮግራሞች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ተማሪዎቻቸውን በውጤታማነት እንዲያስመርቁ እና ሰልጣኞች ለሚጠበቅባቸው ብቃት እንዲተጉ ለማስቻል ይህ የስኮላርሽፕ ማስፈጸሚያ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

### አንቀጽ 5 የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በሀገራችን የስኮላርሽፕ አሰጣጥን ወጪ ቆጣቢ፣ ግልፅ፣ ፍትሀዊ፣ አሳታፊ እና በብቃት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

### አንቀጽ 6 የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሁሉም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በሌሎች ተቋማት እና የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የስኮላርሽፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 7 መርሆዎች

ሀ. ግልፀኝነት

ለ. ፍትሃዊነት

ሐ. ጥራትና አግባብነት

መ. ብቃት

ሠ. ወጪ ቆጣቢ

# ክፍል ሁለት
# የሀገር ውስጥ የስኮላርሽፕ አሰጣጥ

## አንቀጽ 8 ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሀገር ውስጥ ስኮላርሽፕ የመወዳደሪያ መስፈርቶች

1/ ተወዳዳሪው የሙከራ ቅጥር ጊዜውን አጠናቆ ቋሚ የሆነና የሁለት ተከታታይ የስራ አፈፃፀም ውጤት ያለው መሆን አለበት፡፡

2/ ሥልጠናውን አጠናቆ የተመለሰ ሰልጣኝ ግዴታውን ሳይወጣ በሌላ ውድድር መሳተፍ አይችልም፡፡ ነገር ግን የሥልጠናው አስፈላጊነት በተቋሙ አስተዳደር ካውንስል ወይም በአቻ አደረጃጀት ተገምግሞ ከታመነበት የተቀመጠውን ግዴታ ሳያጠናቅቅ ቀሪ ግዴታው ላይ ተጨማሪ ውል ገብቶ ሊማር ይችላል፡፡

3/ አንድ ሰልጣኝ የትምህርትና ሥልጠና ዕድል ካገኘ በኋላ የሚሰራበትን ተቋም ፍቃድ ሳያገኝ ካቋረጠ ለአንድ ዓመት መወዳደር፣ ትምህርት ጀምሮ ማቋረጥ፤ የተሰጠውን ዕድል አለመጠቀም፣ ትምህርት ሳያጠናቅቁ ማቋረጥ አይፈቀድም፡፡

4/ ማንኛውም ሰልጣኝ ሥልጠናውን በተመደበበት ተቋምና በተያዘለት ጊዜ መከታተል ይገባዋል፡፡ ሆኖም ግን በአሳማኝ ምክንያት ትምህርቱን ወይም ሥልጠናውን መከታተል ያልቻለ ከሆነ ከሚመለከተው አካላት በሚቀርበው መረጃ መሰረት ታይቶ ቀጣይ ዓመት እንዲማር ይደረጋል፡፡

5/ በመንግስት ለሚገኝ የሥልጠና ዕድል የመወዳደሪያ ዕድሜ ጣሪያ ለሁለተኛ ዲግሪ 35 እና ለሦስተኛ ዲግሪ ደግሞ 45 ዓመት ይሆናል፡፡

6/ በግል ሙሉ ወጪ ለሚገኝ የትምህርት ዕድል የዕድሜ ጣሪያ አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 9 የሀገር ውስጥ ስኮላርሽፕ ምልመላና መረጣ መስፈርቶች

1/ ለድህረ ምረቃ ሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪ፣ ድህረ ዶክቶራል፣ ስፔሻሊቲና ድህረ ስፔሻሊቲ ፕሮግራም ለሚወዳደሩ የአካዳሚክ ሰራተኞች የማወዳደሪያ መስፈርቶች ባላቸው የትምህርት ዝግጅት፣ ያስመዘገቡት የመመረቂያ ውጤት (CGPA)፣ የስራ ልምድ፣ የሁለት ጊዜ የስራ አፈጻጸም ውጤት፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በልዩ ልዩ



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

የኮሚቴ ነክ ስራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ፣ በጥናትና ምርምር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግር ተሳትፎ፣ በማኅበረሰብ አገልግሎት፣ ኢንዱስትሪ ትስስር ተሳትፎ፣ የሙያ መተዋወቂያ ሥልጠና ተሳትፎ፣ የከፍተኛ ዲፕሎማ ሥልጠና የወሰደ፣ ከተቋሙ ባህርይ አንጻር ተመሳሳይ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች ተሳትፎ እና የማህደር ጥራት ይሆናል (ዝርዝርና ዋጋው በአባሪ ተያይዟል)፡፡

2/ የሚሰጠው የትምህርትና ሥልጠና ዕድል የመምህራንን አቅምና ብቃት ማሳደግ ላይ ቅድሚያ ትኩረት ያደረገ መሆን አለበት፡

3/ ተወዳዳሪዎች የዩኒቨርስቲውን መግቢያ መስፈርቶችን (የመግቢያ ፈተና ማለፍ፣ ለውድድሩ የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ፣ የመመረቂያ ውጤት/CGPA እና በተቋማቱ የተቀመጡ ሌሎች ተጨማሪ የቅበላ መስፈርቶችን) ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፣

4/ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ልዩ የመማር ፍላጎት ላላቸው ተወዳዳሪዎች በህግ የተፈቀደው አዎንታዊ ማበረታቻ በምልመላው ሂደት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፤

5/ የስራ ክፍሉ የተወዳዳሪዎችን ማመልከቻና ማስረጃ በአግባቡ በመያዝ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 የተመለከቱትን መመዘኛዎች ያሟሉትን ተወዳዳሪዎች ለሥልጠና ምልመላና መረጣ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

6/ የስራ ክፍሉ ኃላፊ ተወዳዳሪ በሚሆንበት ጊዜ ለራሱ ጉዳይ ብቻ እንዲነሳ ተደርጎ በምትኩ ጊዜያዊ ሰብሳቢ በመስሪያ ቤቱ ኃላፊ እንዲወከል ይደረጋል፡፡ አንዱ ወይም ሁለቱም የኮሚቴ አባላት ተወዳዳሪ በሚሆኑበት ጊዜ በመስሪያቤቱ የበላይ ኃላፊ አማካኝነት ጊዜያዊ ኮሚቴ እንዲሰየም ይደረጋል፡፡

7/ የስራ ክፍሉ የሥልጠና ምልመላና መረጣ ኮሚቴ የማወዳደሪያ መስፈርቶች አማካኝነት አመልካቾችን በማወዳደር አሸናፊውን በውጤት በመለየት በስራ ክፍሉ ኃላፊ ተፈርሞ ለሚመለከተው አካል ይላካል፡፡ ይህ በተዋረድ ላሉት የስራ ክፍሎችም የሚሰራ ይሆናል፡፡

8/ የሥልጠና ዕድሉ የተሰጠው መስሪያ ቤት/ተቋም የበላይ ኃላፊ በማረጋገጥና በማፅደቅ ለሚመለከተው መስሪያ ቤት በመሸኛ ደብዳቤ ከአስፈላጊ መረጃዎች ጋር እንዲላክ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም መረጃው በተዘጋጀ ቴክኖሎጂ ፕላት ፎርም እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

9/ በማንኛውም ደረጃ ምልመላና መረጣው ከተጠናቀቀ በኋላ የፀደቀው ውጤት ለሚመለከተው አካል በተለያየ ስልቶች ይፋ መሆን ይገባዋል፡፡

10/ የተገኘው ስኮላርሽፕ የጥናቱ መስክ ያልተለየ ከሆነ የማኔጅመንት ካውንስል በሚወስነው ውሳኔ መሰረት ሰራተኞች እንዲወዳደሩ ይደረጋል፡፡

11/ የሥልጠና ዕድል ሲመጣ ተወዳዳሪዎች በኢንተርኔት የሚያመለክቱ ከሆነ የተቋሙን የሥልጠና ፍላጎት ማዕከል በማድረግ የማኔጅመንት ካውንስል በሚወስነው ውሳኔ መሰረት አመልካቾች እንዲወዳደሩ ይደረጋል፡፡

12/ የማኔጅመንት ካውንስል በሚወስነው ውሳኔ መሰረት በግልጽ ማስታወቂያ የሚመለከታቸው ሰራተኞች እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 10 በግል ስለሚገኝ ስኮላርሽፕ

1/ በአንቀፅ 9 የተጠቀሱት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው በግል የተገኘ ስኮላርሽፕ ለውድድር አይቀርብም፡፡

2/ አንድ ሰራተኛ በግሉ በመፃፃፍ በያዘው የትምህርት ደረጃ የተለየ የደረጃ ለውጥ የማያመጣ ስኮላርሽፕ ቢያገኝ ለተቋሙና ለሀገር የሚኖረውን የተለየ ፋይዳ በአሰሪ መስሪያ ቤቱ ሲታመንበት ብቻ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

3/ በግል የተገኘ ስኮላርሽፕ ከመንግሥት ምንም ዓይነት ድጋፍ የማይጠይቅ ከሆነ ከአሠሪ ተቋሙ ምንም የውል ስምምነት ሳይፈጽም መሄድ ይችላል፡፡

4/ ከዚህ ቀደም በተሰጠው ስኮላርሽፕ ዕዳ ካለበት ዕዳው ታሳቢ ተደርጎ የዕድሉ ተጠቃሚ መሆን ይችላል፡፡

5/ በግል የተገኘ ስኮላርሽፕ ከመንግሥት ከድጋፍ ደብዳቤ ጀምሮ ድጋፍ የሚጠይቅ ከሆነ ከአሠሪ ተቋም ጋር ተመልሶ ለማገልገል የውል ስምምነት መፈጸም ይጠበቅበታል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

## አንቀጽ 11 ለሌሎች ተቋማት የሚሰጥ ስኮላርሽፕ የመወዳደሪያ መስፈርቶች

1/ ተወዳዳሪዎች የዩኒቨርስቲውን የቅበላ መስፈርቶችን (የመግቢያ ፈተና ማለፍ፣ ለውድድሩ የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ፣ የመመረቂያ ውጤት /CGPA እና በተቋማቱ የተቀመጡ ተጨማሪ የቅበላ መስፈርቶችን) ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፣

2/ የሚሰጠው የትምህርት ዕድል በትምህርት ዘመኑ ያለውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቅባለ አቅም እና የላኪ ተቋማት የበጀት ድጋፍ ታሳቢ በማድረግ የሚከናወን ይሆናል፣

3/ በዚህ መመሪያ ከተቀመጡ መስፈርቶች በተጨማሪ ለፌደራልና ለክልል ሴክተር መስሪያቤት ሰራተኞች የትምህርትና ሥልጠና ዕድል የማወዳደሪያ መስፈርቶች ነጥብ አሰጣጥ በአገሪቱ የሰው ሀብት ልማት ድንጋጌዎችና በየመስሪያ ቤቶቹ የትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ መመሪያ መሰረት የሚከናወን ይሆናል፤

4/ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ አከባቢዎች እንደ ሀገር የተቀመጡ አዎንታዊ ማበረታቻዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

5/ የስኮላርሽፕ አሰጣጥ ፍትሃዊና ግልጽ በሆነ መንገድ በኮታ ለተቋማት የሚከፋፈል ይሆናል፡፡

6/ በመንግስት ለሚገኝ የስኮላርሽፕ የመወዳደሪያ እድሜ ጣሪያ ለሁለተኛ ዲግሪ 35 እና ለሦስተኛ ዲግሪ ደግሞ 45 ዓመት ይሆናል፡፡

7/ በግል ሙሉ ወጪ ለሚገኝ የስኮላርሽፕ የዕድሜ ጣሪያ አይኖረውም፡፡

8/ ሴት አመልካቾች ላኪው እና ተቀባይ ተቋማት ያስቀመጡትን አነስተኛ መስፈርት ማሟላት እንደ ተጠበቀ ሆኖ ቅድሚያ እንዲያገኙ ይደረጋል።

## አንቀጽ 12 የሌሎች ተቋማት ስኮላርሽፕ የምልምላና መረጣ መስፈርቶች

1/ የስኮላርሽፕ ሲመጣ ግልጽና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድልድል ተሰርቶ የሚመለከታቸው ተቋማት እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

2/ የትምህርትና ሥልጠና ጥናት መስኩ የሚያስቀምጣቸው መሰረታዊ መመልመያ መስፈርቶች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተግባራዊ ይደረጋሉ፤



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

3/ የሚመለከታቸው ተቋማት በተሰጣቸው ኮታ መሰረት የማወዳደሪያ መስፈርቶችን ተጠቅመው ያለፉትን ተወዳዳሪዎች የትምህርት ማስረጃዎችና ሌሎች ሰነዶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባሉ፤

4/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወዳዳሪዎችን የትምህርት ማስረጃ በማጣራት የተቀመጡ መስፈርቶች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ የሥልጠና እድሉን ለሰጠው አካል ይፋ ያደርጋል፤

5/ የተገኘው የትምህርትና ሥልጠና ዕድል የጥናት መስክ ያልተለየ ከሆነ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል፤

## ክፍል ሶስት
## የውጭ ሀገር የስኮላርሽፕ አሰጣጥ

### አንቀጽ 13 ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለውጭ ሀገር ስኮላርሽፕ የመወዳደሪያ መስፈርቶች

1/ ተወዳዳሪው የሙከራ ቅጥር ጊዜውን አጠናቆ ቋሚ የሆነና የሁለት ተከታታይ የስራ አፈፃፀም ውጤት ያለው መሆን አለበት፡፡

2/ ሥልጠናውን አጠናቆ የተመለሰ ሰልጣኝ ግዴታውን ሳይወጣ በሌላ ውድድር መሳተፍ አይችልም፡፡ ነገር ግን የሥልጠናው አስፈላጊነት በተቋሙ አስተዳደር ካውንስል ወይም በአቻ አደረጃጀት ተገምግሞ ከታመነበት የተቀመጠውን ግዴታ ሳያጠናቅቅ ቀሪ ግዴታው ላይ ተጨማሪ ውል ገብቶ ሊማር ይችላል፡፡

3/ አንድ ሰልጣኝ ስኮላርሽፕ ካገኘ በኋላ የሚሰራበትን ተቋም ፍቃድ ሳያገኝ ካቋረጠ በቀጣይ ውድድር ለአንድ ዓመት መወዳደር አይችልም፣

4/ ስኮላርሽፕ ያገኘ ሰልጣኝ የተሰጠውን ዕድል አለመጠቀም እንዲሁም ትምህርት ሳያጠናቅቅ ማቋረጥ አይፈቀድም፡፡

5/ ያለተቋሙ ፍቃድ ካቋረጠ ለስኮላርሽፕ የወጣውን ወጪ በገባው ውል ስምምነት መሰረት በገንዘብ ወይም በአገልግሎት ይተካል፡፡

6/ ማንኛውም ሰልጣኝ ሥልጠናውን በተመደበበት ተቋምና በተያዘለት ጊዜ መከታተል ይገባዋል፡፡ ሆኖም ግን በአሳማኝ ምክንያት ትምህርቱን ወይም ሥልጠናውን መከታተል ያልቻለ ከሆነ ከሚመለከተው አካላት በሚቀርበው መረጃ መሰረት ታይቶ ቀጣይ ዓመት እንዲማር ይደረጋል፡፡

7/ በመንግስት ለሚገኝ ስኮላርሽፕ የመወዳደሪያ ዕድሜ ጣሪያ ለሁለተኛ ዲግሪ 35 እና ለሦስተኛ ዲግሪ ደግሞ 45 ዓመት ይሆናል፡፡

8/ በግል ሙሉ ወጪ ለሚገኝ የውጭ ሀገር የትምህርት ዕድል የዕድሜ ጣሪያ የሚወሰነው በአሰልጣኙ ተቋም ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 14 ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚሰጥ የውጭ ሀገር ስኮላርሽፕ ምልመላና መረጣ መስፈርቶች

1/ ለሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪ፣ ለድህረ ዶክቶራል፣ ለስፔሻሊቲና ለድህረ ስፔሻሊቲ ፕሮግራም ለሚወዳደሩ የአካዳሚክ ሰራተኞች የማወዳደሪያ መስፈርቶች ባላቸው የትምህርት ዝግጅት ያስመዘገቡት የመመረቂያ ውጤት (CGPA)፣ የስራ ልምድ፣ የሁለት ጊዜ የስራ አፈጻጸም ውጤት፣ በከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በልዩ ልዩ የኮሚቴ ነክ ስራዎች፣ በጥናትና ምርምር/ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የማኅበረሰብ ጉድኘት/ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን፣ የሙያ መተዋወቂያ ሥልጠና፣ የከፍተኛ ዲፕሎማ ሥልጠና/ከተቋሙ ባህርይ አንጻር ተመሳሳይ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ላይ ባላቸው ንቁ ተሳትፎ እና የማህደር ጥራት ይሆናል (ለእያንዳንዱ መስፈርት የተሰጠው ክብደት በአባሪ ተያይዟል)።

2/ የሚሰጠው ስኮላርሽፕ የመምህራንን አቅምና ብቃት ማሳደግ ላይ ቅድሚያ ትኩረት ያደረገ መሆን አለበት።

3/ የተወዳዳሪዎች የትምህርት ደረጃ እና የትምህርት ዝግጅት በየትምህርት ደረጃ የተቀመጠውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቀጣይ የትምህርት ደረጃ የቅበላ መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል።

4/ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ልዩ የመማር ፍላጎት ላላቸው ተወዳዳሪዎች በህግ የተፈቀደው አዎንታዊ ማበረታቻ በምልመላው ሂደት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል።

5/ ተቋሙ የተወዳዳሪዎችን ማመልከቻና ማስረጃ በአግባቡ በመያዝ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 የተመለከቱትን መመዘኛዎች ያሟሉትን ተወዳዳሪዎች ለስኮላርሽፕ ምልመላና መረጣ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

6/ የኮሚቴው ሰብሳቢ ተወዳዳሪ በሚሆንበት ጊዜ ለራሱ ጉዳይ ብቻ እንዲነሳ ተደርጐ በምትኩ ጊዜያዊ ሰብሳቢ በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንዲወከል ይደረጋል፡፡

7/ አንድ የኮሚቴ አባል ወይም ዘመዱ ተወዳዳሪ በሚሆንበት ጊዜ ከኮሚቴ አባልነት በጊዜያዊነት እንዲወጣ ይደረጋል።

8/ ሁለት እና ከዚያ በላይ የኮሚቴ አባላት ተወዳዳሪ በሚሆኑበት ጊዜ በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ አማካኝነት ጊዜያዊ ኮሚቴ እንዲሰየም ይደረጋል፡፡



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

9/ የተቋሙ የስኮላርሽፕ ምልመላና መረጣ ኮሚቴ በማወዳደሪያ መስፈርቶች አማካኝነት አመልካቾችን አወዳድሮ አሸናፊውን በውጤት በመለየት በተቋሙ ኃላፊ ተፈርሞ ለሚመለከተው አካል ይላካል፡፡ ይህ በተዋረድ ላሉት የስራ ክፍሎችም የሚሰራ ይሆናል፡፡

10/ የተሰጠው ስኮላርሽፕ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ በማረጋገጥና በማጽደቅ ለሚመለከተው መስሪያ ቤት በመሸኛ ደብዳቤ ከአስፈላጊ መረጃዎች ጋር እንዲላክ ያደርጋል፡፡

11/ በማንኛውም ደረጃ ምልመላና መረጣው ከተጠናቀቀ በኋላ የጸደቀው ውጤት ለሚመለከተው አካል በተለያየ ስልቶች ይፋ መሆን ይገባዋል፡፡

12/ በተገኘው ስኮላርሽፕ የጥናቱ መስክ ያልተለየ ከሆነ የተቋሙ የመምህራን ልማት ዕቅድን መሰረት ባደረገ መልኩ በማኔጅመንት ካውንስል በሚወስነው ውሳኔ መሰረት አካዳሚክ ሰራተኞቹ እንዲወዳደሩ ይደረጋል፡፡

13/ የስኮላርሽፕ ዕድል ሲሰጥ ተወዳዳሪዎች በበይነ መረብ (Online) የሚያመለክቱ ከሆነ የተቋሙን ፍላጎት ማዕከል በማድረግ የማኔጅመንት ካውንስል በሚወስነው ውሳኔ መሰረት አመልካቾች እንዲወዳደሩ ይደረጋል።

14/ በንዑስ አንቀጽ 12 እና 13 ላይ በተመለከተ የተቋሙ ማኔጅመንት ካውንስል በሚወስነው ውሳኔ መሰረት በግልጽ ማስታወቂያ የሚመለከታቸው ሰራተኞች እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡

15/ ለውጭ ሀገር ስኮላርሽፕ የሚወዳደሩ የሴት አመልካቾች ከወሊድ ጋር በተገናኘ አስተማሪው ተቋም/ሀገር በሚያወጣው ህግ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 15 በግል ስለሚገኙ የአጭርና የረጅም ጊዜ ስኮላርሽፕ**

1/ በግል የተገኘ የአጭርና የረጅም ጊዜ ስኮላርሽፕ ለውድድር አይቀርብም፡፡

2/ በግል በመፃፃፍ በያዘው የትምህርት ደረጃ አቻ (የተለየ የደረጃ ለውጥ የማያመጣ) ትምህርት ለመማር የሚፈልግ ሰራተኛ ለተቋሙና ለሀገር የሚኖረውን የተለየ ፋይዳ በአሰሪ መስሪያ ቤቱ ሲታመንበት ብቻ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

3/ በግል የተገኘ ስኮላርሽፕ ከመንግሥት ምንም ዓይነት ድጋፍ የማይጠይቅ ከሆነ ከአሠሪ ተቋሙ ምንም የውል ስምምነት ሳይፈጽም መማር ይችላል፡፡



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

4/ በግል የተገኘ ስኮላርሽፕ ከመንግሥት የድጋፍ ደብዳቤ ጀምሮ ድጋፍ የሚጠይቅ ከሆነ ከአሠሪ ተቋም ጋር ተመልሶ ለማገልገል የውል ስምምነት ፈጽሞ መሄድ ይጠበቅበታል፡፡

**አንቀፅ 16 ለበትረ ሳይንስ ፕሮግራም ስኮላርሽፕ ለውድድር የሚያበቁ መመዘኛዎች**

1/ አስራ ሁለተኛ ክፍል አጠናቀው በተመደበቡት ዩኒቨርስቲ አንደኛ ዓመት ላይ ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ብቻ፣

2/ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ፣ በሁለተኛ ዲግሪና በሦስተኛ ዲግሪ በሳይንስ፣ በምህንድስናና ቴክኖሎጂ በማስተማር ላይ ለሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት መምህራን፣

3/ ለሁለተኛ ዲግሪና በላይ ስኮላርሽፕ ተወዳዳሪዎች ዕድሉ የሚሰጣቸው አስፈላጊ መረጃዎችን ማለትም የትምህርት የወጪ መጋራት እና የትምህርት መስኩ የሚጠይቃቸውን መረጃዎችን ማቅረብ የሚችሉ፣

4/ በውጭ አገራት ለሚሰጡ ስኮላርሽፕ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ /በተቀባይ ተቋማት የሚሰጠውን ፈተና ማለፍ የሚችሉ እና

5/ ተማሪዎች ምልመላና መረጣውን ካለፉ ከላኳቸው ተቋማት ጋር አስፈላጊውን የውል ስምምነት በማድረግ ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመለሱ ቅጥር መፈፀም ይጠበቅባቸዋል፡፡

**አንቀጽ 17 ለበትረ ሳይንስ ፕሮግራም የሚሰጥ ስኮላርሽፕ ዕድል የማወዳደሪያ ነጥቦች**

በዚህ ፕሮግራም የዕድሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ አመልካቾች፡-

1/ ከዩኒቨርሲቲዎች በአንደኛ ዓመት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ የተፈጥሮ ሳይንስ (ሳይንስ፣ ምህንድስናና ቴክኖሎጂ) ተማሪዎች፣

2/ መምህራን/ተመራማሪዎች በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ እና በኢንጂነሪንግ የሙያ መስኮች በልዩ ሁኔታ በሁለተኛና በሶስተኛ ዲግሪ ፕሮግራሞችና በአጫጭር ሥልጠናዎች ከውጭ ሀገራት ዩኒቨርሲቲዎች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን ትኩረት በማድረግ ተሞክሮዎችን ወደ አገር ቤት ለማምጣት ተነሳሽነትና ጉጉት ያላቸው፣



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

3/ በውድድሩ ተመርጠው ለትምህርት የሚላኩ ሠልጣኖች ከላኪው ተቋም ጋር ውል ስምምነት የሚፈርሙ መሆን ይጠበቅባቸዋል፣

4/ ስኮላርሽፑ በመንግሥት በተመረጡ ዩኒቨርስቲዎች እና ፕሮግራሞች ብቻ የሚሰጥ ይሆናል፤

5/ በመንግስት ለሚገኝ ስኮላርሽፕ የመወዳደሪያ ዕድሜ ጣሪያ ለሁለተኛ ዲግሪ 35 እና ለሶስተኛ ዲግሪ ደግሞ 45 ዓመት ይሆናል፡፡

6/ ለስኮላርሽፕ የሚወዳደሩ የሴት አመልካቾች ከወሊድ ጋር በተያያዘ አስተማሪው ተቋም/ ሀገር በሚያወጣው ህግ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 18 ለበትረ ሳይንስ ፕሮግራም የሚሰጥ ስኮላርሽፕ የምልምላና መረጣ መስፈርቶች

1/ ተወዳዳሪዎች የዩኒቨርስቲውን መግቢያ መስፈርቶችን (የመግቢያ ፈተና ውጤት፣ ለውድድሩ የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ፣ የመመረቂያ ውጤት/CGPA እና በተቋማቱ የተቀመጡ ተጨማሪ የቅበላ መስፈርቶችን) ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።

2/ ስኮላርሽፕ ሲመጣ ግልጽና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚሰጠው ኮታ መሰረት ድልድል ተሰርቶ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡

3/ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ልዩ የመማር ፍላጎት ላላቸው ተወዳዳሪዎች በህግ የተፈቀደው አዎንታዊ ማበረታቻ በምልመላው ሂደት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል።

4/ የትምህርት ወይም ጥናት መስኩ የሚያስቀምጣቸው መሰረታዊ መመልመያ መስፈርቶች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተግባራዊ ይደረጋሉ።

5/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተሰጣቸው ኮታ መሰረት የማወዳደሪያ መስፈርቶችን ተጠቅመው ያለፉትን ተወዳዳሪዎች የትምህርት ማስረጃዎችና ሌሎች ሰነዶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባሉ።

6/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወዳዳሪዎችን የትምህርት ማስረጃ በማጣራት የተቀመጡ መስፈርቶች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ለሚመለከታቸው አካላት ይፋ ያደርጋል፤

7/ የተገኘው ስኮላርሽፕ የጥናት መስክ ያልተለየ ከሆነ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል፤

# ክፍል አራት
# ተግባርና ኃላፊነት

## አንቀጽ 19 የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

1. ትምህርት ሚኒስቴር

ሀ. በተለያዩ ሀገራት ካሉ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላዎች ጋር በመቀናጀት የረጅም እና የአጭር ጊዜ ስኮላርሽፕ በማፈላለግ የመግባቢያ ስምምነቶችን ይፈራረማል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል።

ለ. የስኮላርሽፕ መስፈርቶችን፣ ስታንዳርዶችን እና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ያሻሽላል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፡፡

ሐ. ስኮላርሽፕ ሲገኝ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለተቋማት በሚሰጠው ኮታ መሰረት ተማሪዎችን እንዲልኩ ለተቋማት የስኮላርሽፕ ማስታወቂያዎችን ይልካል፡፡

መ. ከላኪ ተቋማት በውድድሩ የተላኩ ሰልጣኞች መረጃ የትምህርት ዕድሉን ለሰጡ ተቋማት በስምምነቱ መሰረት በSoft /በHard Copy/ በማደራጀት የተማሪዎችን መረጃ ይልካል፤ ለክትትል እንዲያመች ለኤምባሲዎች ያሳውቃል፡፡

ሠ. የስኮላርሽፕ ዕድል ሲፈቀድ የተማሪዎችን ዝርዝር መረጃ ወደ አወዳደሩት ተቋማት ይልካል፡፡

ረ. ዕድሉን ያገኙ ተማሪዎች ከአሰሪ ተቋማት ጋር የውል ስምምነት መግባታቸው ሲረጋገጥ የመገጣጠሚያ ደብዳቤ ስኮላርሽፕ ወደ ሰጠው ተቋም ይልካል፡፡

ሰ. ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ የገንዘብ ክፍያዎችን በኤምባሲዎች በኩል እንዲፈጸም ይልካል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

ሸ. ለተማሪዎች የሚሰጡ ጥቅማጥቅሞችን በየጊዜው በማጥናት ካለው የኑሮ ሁኔታ አንፃር እንዲከፍሉ ለሚመለከታቸው አካላት ለውሳኔ ያቀርባል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ቀ. በውጭ ሀገራትና በሀገር ውስጥ የሚሰጥ ስኮላርሽፕ ውጤታማነትን በማጥናት ማስተካከያዎችን ያደርጋል።

በ. በውጭ ሀገራት ስኮላርሽፕ አጠናቀው የሚመለሱ ተማሪዎችን የመገጣጠሚያ ደብዳቤ ለላኪው ተቋም ይጽፋል፤መረጃ ያደራጃል፤ ይከታተላል፡፡



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ተ. እንደ አስፈላጊነቱ ሚኒስቴሩ ከላኪና አሰልጣኝ ተቋማት ጋር በተማሪዎች የትምህርት ሁኔታ ዙሪያ በጋራ ወይም በተናጠል ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።

ቸ. የበትረሳይንስ ፕሮግራሞች ስኮላርሽፕ በማፈላለግ አሰልጣኝ ተቋማትን ከኤምባሲዎች ጋር ይመርጣል፣

ኀ. ለስኮላርሽፕ አመልካቾች ስኮላርሽፕ የሚሰጠው በጀት መኖሩ ሲያረጋግጥ ብቻ ይሆናል፡፡

## 2. ላኪ ተቋም

ሀ. የዚህን መመሪያ የስኮላርሽፕ መስፈርት ወይም ስታንዳርድ በግልጽ ለተወዳደሪዎች ያሳውቃል።

ለ. የስኮላርሽፕ ውድድሩ ጥራትን ባማከለ አግባብ ግልጽ፣ ፍትሃዊና አሳታፊ በሆነ መንገድ ወቅቱን ጠብቆ ምልመላ መደረጉን በቃለ ጉባኤ በማስደገፍ የተመረጡ ተማሪዎችን መረጃ አጠናቅሮ ለትምህርት ሚኒስቴር በSoft /በHard Copy/ በበይነ መረብ ይልካል።

ሐ. ለስኮላርሽፕ የተላኩ ተማሪዎች በተቀመጠው የቆይታ ጊዜ መሠረት ትምህርታቸውን ማጠናቀቅ መቻላቸውን ይከታተላል፣ ያላጠናቀቁትን አስመልክቶ ከአሰልጣኝ ተቋም ማብራሪያ በመጠየቅ ችግሩ እንዲፈታ ያደርጋል።

መ. አንድ ተማሪ አሳማኝ በሆነ ምክንያት ትምህርቱን በተቀመጠው የቆይታ ጊዜ ማጠናቀቅ ሳይችል ሲቀር ከአሰልጣኝ ተቋም ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሰልጣኙ የመደበኛ ስራውን እየሰራ ትምህርቱን እንዲያጠናቅቅ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ለሚኒስቴሩ ያሳውቃል።

ሠ. በመመሪያው የተለዩ የተማሪዎች መብትና ግዴታዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

ረ. ስኮላርሽፕ ያገኙትን ሰራተኞች የውል ስምምነት፣ ክሊራንስ፣ የወጪ መጋራት ስለማጠናቀቃቸው በማረጋገጥ ዝርዝር መረጃ ለሚኒስቴሩ ይልካል፡፡

ሰ. ስኮላርሽፕ ለማስጨረስ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ የደርሶ መልስ የትራንስፖርት፣ ቪዛ ለማስጨረስ እና የትምህርት ማስረጃ ለማረጋገጥ የሚወጡ ወጪዎችን ይሸፍናል፡፡

ሸ. የስኮላርሽ ዕድል ያገኘ ተማሪ የትምህርት ጊዜ ቆይታ የማራዘም ዕድል ተሰጥቶት ከአሰልጣኝ ተቋማት በአካደሚክ ችግር ምክንያት ቢሰናበት እና ትምህርቱን በገዛ ፈቃዱ የሚያቋርጥ ከሆነ በውል ስምምነት መሠረት የከፍተኛ ትምህርት መምህር ሆኖ መቀጠል አይችልም፡፡ ለትምህርት የወጣውን ወጪ በውሉ መሰረት ለመንግስት ተመላሽ ያደርጋል፡፡

ቀ. በየሴሚስተሩ ተማሪዎች ያሉበትን ደረጃ (Academic Status) መረጃ በመያዝ ለተለያዩ ውሳኔዎች በግብዓትነት ይጠቀማል፣

3. አሰልጣኝ ተቋም

ሀ. በትምህርት ሚኒስቴር በሚደረገው የተማሪዎች ምደባ መሰረት ባላቸው ሙሉ አቅም ተቀብለው ያሰለጥናል።

ለ. አሰልጣኝ ተቋሙ ለማስተማርና ለማሰልጠን የተቀበላቸውን ተማሪዎች የትምህርት ሁኔታ ይከታተላል፣ የየሴሚስተር ውጤታቸውን ለላኪ ተቋማት ያሳውቃል፡፡

ሐ. ለደረጃው ብቁ የሆነ የሰው ሀብትና ሌሎች ግብዓቶች በማሟላት የመማር ማስተማርና የምርምር ሂደቱ የጥራት ደረጃውን ጠብቆ እንዲከናወን ያደርጋል፡፡

መ. ለመማር ማስተማርና ለምርምር ድጋፍ የሚያወጣውን ወጪ መረጃ በመያዝ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፡፡

ሠ. ዝቅተኛ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ በማድረግ ትምህርታቸውን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ እንዲያጠናቅቁ ያደርጋል፡፡

ረ. በውጤት ማነስ ምክንያት የሚሰናበቱ ተማሪዎች/ ሰልጣኞችን ሁኔታ አስመልክቶ ከተጨባጭ መረጃዎች ጋር ለላካቸው ተቋም በወቅቱ ያሳውቃል፡፡

ሰ. በመንግስት በተወሰነው መሰረት ለመማር ማስተማርና ለምርምር የበጀት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ሸ. ተማሪዎች ትምህርታቸውን በወቅቱ እንዳያጠናቅቁ ተግዳሮት የሆኑባቸውን ችግሮች በመለየት ለሚመለከታቸው አካላት ማብራሪያ ያቀርባል፣ መፍትሄም እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

ቀ. አማካሪ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮችን በጊዜ የመመደብ ኃላፊነት ይኖርበታል።



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

## 4. የሰልጣኞች መብትና ግዴታ

### 4.1. የሰልጣኞች መብት

ሀ. ስኮላርሽፕ ማስፈጸሚያ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ደመወዝ እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት፣

ለ. የውጭ ሀገር ሰልጣኞች በሥልጠና ቆይታ ጊዜ በየወሩ የግማሽ ደመወዝ ክፍያ የሚያገኙ ሆኖ በሀገር ውስጥ የሚማሩ ከሆነ ግን ሙሉ የደመወዝ ክፍያ የማግኘት፣

ሐ. ማንኛውም ተማሪ የአሰራር መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት በሥራ ላይ ለሚገኙ የአካዳሚክ ሰራተኞች በየጊዜው የሚሰጡ ጥቅማጥቅሞች የማግኘት፣

መ. በሥልጠና ወቅት ቤተ ሙከራዎችን እና ወርክሾፖችን የመጠቀም እንዲሁም ሌሎች ለሥልጠና የሚያስፈልጉ ድጋፎችን በነፃ ወይም በክፍያ የማግኘት፣

ሠ. ስኮላርሽፑን አጠናቆ ሲመለስ የተቋሙ አሰራር በሚፈቅደው መሰረት ደረጃው በሚመጥን ቦታ የመመደብ፣ ለቦታው የተፈቀደውን ጥቅማጥቅም የማግኘት፤

ረ. በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ትምህርት ወቅት የሚፈጠር እርግዝና/ወሊድን በተመለከተ ተማሪዎቹ በ Withdrawal ወደ ላኪው ተቋም ተመልሰው ሙሉ ደመወዝ የማግኘት፤ የወሊድ ፈቃዳቸው ሲጠናቀቅ ትምህርታቸውን ካቆሙበት የመቀጠል፣

ሰ. የትምህርት አታሼ በሌላቸው ሀገራት ተማሪዎች በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና በኤምባሲዎቹ ድጋፍና ክትትል የማግኘት፣

ሸ. ተማሪው በግሉ ያገኘው የውጭ አገር ስኮላርሽፕ ላኪው ተቋም ካመነበት ለአጭር ጊዜ ስኮላርሽፕ ትራንስፖርት ወጪ ስፖንሰርሽፕ የሰጠው አካል የማይሸፍን ከሆነ የደርሶ መልስ ትራንስፖርት እና የቪዛ ማስፈፀሚያ የማግኘት፣

ቀ. የትምህርት መረጃውን ዋናውን በተቋሙ አሰራር መሰረት ለሚመለከተው ክፍል ሲያስረክብ የመተማመኛ ሰነድ የማግኘት፣

በ. ተማሪው የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሙ በመቋረጡ ወይም በሌላ አስገዳጅ ሁኔታ መቀጠል ካልቻለና ትምህርቱ ለሀገር ልማት ያለው ጠቀሜታ ተገምግሞ



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ሲፈቀድ የመጀመሪያውን ሴሚስተር ትምህርት ከማጠናቀቁ በፊት የመቀየር መብት ይኖረዋል፡፡

### 4.2 የተማሪው ግዴታዎች

ሀ. በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ትምህርቱን ማጠናቀቅ፣

ለ. ያለበቂ ምክንያት ትምህርቱን አለማቋረጥ፣ ከቋረጠም ለቀጣይ አንድ ዓመት በሌሎች ዕድሎች አለመሳተፍ፣

ሐ. ትምህርቱን ያለበቂ ምክንያት ካቋረጠ ያባከነው ወጪ ተሰልቶ የመክፈል ወይም ተጨማሪ ውል የመግባት፣

መ. ትምህርቱ የወሰደበትን ጊዜ እጥፍ ተመልሶ የማገልገል፣ ማገልገል የማይፈልግ ከሆነ ደመወዝን ጨምሮ የወጣውን ወጪ ከነቅጣቱ የመክፈል፣ መልቀቂያ ቢጠይቅ በውሉ መሰረት ያልሰራባቸው ጊዜያት ተሰልቶ ክፍያ የመፈጸም፣

ሠ. በየሴሚስተሩ የደረሰበትን ደረጃ (Status or progress report) ለላከው ተቋም በጽሁፍ የማሳወቅ፣ ተማሪው ስኮላርሺፑን ሳያጠናቅቅ ሌላ ትምህርት በዚያው ቢፈቀድለት ለቀጣዩ ዕድል ውል ሲይዝ ከዚያ በፊት ያልተወጣውን የውል ግዴታ ጨምሮ የመፈረም፣

ረ. ለሚከፈለው የደመወዝ፣ ሌሎች የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፎች ተመጣጣኝ ዋስ የማቅረብ፣

ሰ. ለስኮላርሽፕ የተላከ ሰልጣኝ ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ የመመረቂያ ጽሑፉን ቅጂ ለብሔራዊ ቤተመዛግብት/National Archieve/ እና ለላኪ ተቋም መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

ሸ. በሦስተኛ ዲግሪ መርሀ ግብር በሀገር ውስጥ ዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን የሚከታተል መምህር በአገልግሎት የማይያዝ 3 Cr.hr የማስተማር፣

ቀ. የእጩ ተማሪ ውጤት በአሰልጣኝ ተቋም እስኪታወቅ ድረስ ለውጭ ሀገር ለ6 ወራት እና ለሀገር ውስጥ ለ3 ወራት በሌላ ስኮላርሽፕ ውድድር መሳተፍ የማይችል መሆኑ፣

በ. በውጭ ሀገር ሥልጠና የተገኘውን ዋናውን የትምህርት ማስረጃ በተገባው ውል እና በተቋሙ አሰራር መሰረት ለሚመለከተው ክፍል የማስረከብ፣



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ተ. ለሁለተኛ ዲግሪ ከሁለት ጊዜ በላይ ዕድል ተሰጥቶት መቀጠል ያልቻለ ሰልጣኝ በመማር ማስተማር ስራው መቀጠል የማይችል መሆኑ፣

ቸ. ትምህርት ከተጀመረ በኋላ የትምህርት መስክ መቀየር የማይቻል መሆኑ፣

ኀ. በግል ለተገኘ የውጭ ሀገር ስኮላርሽፕ የትምህርቱ ጠቀሜታ በሚመለከተው አካል ከታመነበት ሰልጣኙ ተመልሶ ሊሰራ በተስማማበት የስራ ክፍል የሚያገለግል መሆኑ፣

ነ. ሴት ተማሪ የወሊድ ፈቃድ በምትወጣበት ወቅት የስኮላርሽፕ አበልና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን መጠየቅ የማትችል መሆኑ፣

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 20 የተሻሩ መመሪያዎችና ሰርኩላሮች

1/ ከዚህ በፊት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የስኮላርሽፕ ማስፈፀሚያ ሆኖ ሲያገለግል የነበረው መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

2/ ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### አንቀጽ 21 መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ የስኮላርሽፕ ማስፈፀሚያ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ በሚኒስቴሩ ሊያሻሻል ይችላል፡፡

### አንቀጽ 22 መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

መመሪያው በሚኒስትሩ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)

የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ሚኒስትር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

## የሚከተሉት አባሪዎች የመመሪያው አካል ናቸው፡፡

## አባሪዎች

### አባሪ 1 የስኮላርሽፕ ወጪ አሸፋፈን

ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ ተማሪዎች የሚሰጥ ጥቅማ ጥቅምና አገልግሎቶች በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገራት በመንግስትና በአጋር አካላት ድጋፍ ለሚሰጠው ስኮላርሽፕ የሚሰጡ ጥቅማ-ጥቅሞችና ዋና ዋና አገልግሎቶች ከታች በሠንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

| የስኮላርሽፕ ዓይነት | የትምህርት ደረጃ | የወጪው ዓይነት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ለትምህርትክፍያ (Tution Fees) | ለትራንስፖርት ክፍያ | ለመኖሪያ አበል | የምርምር ወጪ | ለጽህፈት፣ ለጽህፈት መሳሪያ ግዥና የፎቶ ኮፒ አገልግሎት |
| ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት አካዳሚክ ሠራተኞች በውጭ ሀገራት የሚሰጥ ስኮላርሽፕ | 2ኛ ዲግሪ | በዓመት በአማካይ $5,000 | በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ የአንድ ጊዜ ደርሶ መልስ የአውሮፕላን ትኬት | በወር $350 | በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚሸፈን ለማህበራዊ ሳይንስ $504*2 እና ለተፈጥሮ ሳይንስ $504*2 | |
| | 3ኛ ዲግሪ | በዓመት በአማካይ $5,000 | በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ የሁለት ጊዜ ደርሶ መልስ የአውሮፕላን ትኬት | በወር $350 | በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚሸፈን ለማህበራዊ ሳይንስ $504*3 እና ለተፈጥሮ ሳይንስ $504*4 | |
| ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት አካዳሚክ ሠራተኞች የሚሰጥ የሀገር ውስጥ ስኮላርሽፕ | 2ኛ ዲግሪ | በሚኒስቴር መ/ቤቱ ይሸፈናል፣ | በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ በወር ለአዲስ አበባ ብር 250፡ ከአዲስ አበባ ውጭ 150 | በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ ለአዲስ አበባ ብር 1,000 ፤ ከአዲስ አበባ ውጪ 700 | በአስተማሪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ ለተፈጥሮ ሳይንስ ብር 25,000፡ ለማህበራዊ ሳይንስ 15,000 | በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ በየወሩ 500 ብር |
| | 3ኛ ዲግሪ | በሚኒስቴር መ/ቤቱ ይሸፈናል፣ | በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ በወር ለአዲስ አበባ ብር 250፡ ከአዲስ አበባ ውጭ 150 | በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ ለአዲስ አበባ ብር 1,000 ፤ ከአዲስ አበባ ውጪ 700 | በአስተማሪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ ለተፈጥሮ ሳይንስ ብር 60,000፡ ለማህበራዊ ሳይንስ ብር 45,000፡ | በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ በየወሩ 500 ብር |
| ለግል ከፍተኛ ትምህርት አካዳሚክ ሠራተኞች የሚሰጥ የሀገር ውስጥ ስኮላርሽፕ | 2ኛና 3ኛ ዲግሪ | በሚኒስቴር መ/ቤቱ ይሸፈናል፡ | በሰልጣኙ/በላኪው ተቋም ይሸፈናል | በሰልጣኙ/በላኪው ተቋም ይሸፈናል | በላኪው ተቋም ይሸፈናል | በሰልጣኙ/በላኪው ተቋም |
| ለሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች የሚሰጥ የሀገር ውስጥ ስኮላርሽፕ | 2ኛና 3ኛ ዲግሪ | በሚኒስቴር መ/ቤቱ ይሸፈናል፡ | በሰልጣኙ/በላኪው ተቋም ይሸፈናል | በሰልጣኙ/በላኪው ተቋም ይሸፈናል | በሚኒስቴሩ ይሸፈናል | በሰልጣኙ/በላኪው መ/ቤት |
| ለበትረ ሳይንስ ፕሮግራም የሚሰጥ የውጭ ሀገራት ስኮላርሽፕ | ቅድመ ምረቃ | በስምምነቱ መሠረት | በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ የአንድ ጊዜ ደርሶ መልስ የአውሮፕላን ትኬት | በወር $350 | | ለመኖሪያ እና ለመሳሰሉት ከተቀመጠ ወጪ |
| | 2ኛ ዲግሪ | በስምምነቱ መሠረት | በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ የአንድ ጊዜ ደርሶ መልስ የአውሮፕላን ትኬት | በወር $350 | በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚሸፈን ለማህበራዊ ሳይንስ እና ለተፈጥሮ ሳይንስ $504*2 | |
| | 3ኛ ዲግሪ | በስምምነቱ መሠረት | በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ የሁለት ጊዜ ደርሶ መልስ የአውሮፕላን ትኬት | በወር $350 | በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚሸፈን ለማህበራዊ ሳይንስ $504*3 እና ለተፈጥሮ ሳይንስ $504*4 | |

ማሳሰቢያ፡- በአባሪ 4 ሌሎች ዝርዝር የወጪ መረጃዎች እንደአስፈላጊነታቸው ቀርበዋል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

አባሪ 2

1/ ለመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት ለሚወዳደሩ የአካዳሚክ ሰራተኞች የማወዳደሪያ መስፈርቶች ነጥብ አሰጣጥ

| | |
|---|---|
| ሀ. CGPA | 30% |
| ለ. ለስራ ልምድ | 15% |
| ሐ. የስራ አፈጻጸም ውጤት | 50% |
| መ. የማህደር ጥራት | 5% |

2/ ለ2ኛ ዲግሪ ትምህርት ለሚወዳደሩ የአካዳሚክ ሰራተኞች የማወዳደሪያ መስፈርቶች ነጥብ አሰጣጥ

2.1 ለዩኒቨርሲቲ መምህራን የነጥብ አሰጣጥ

| | |
|---|---|
| ሀ. CGPA | 30% |
| ለ. ስራ ልምድ | 5% |
| ሐ. የስራ አፈጻጸም ውጤት | 45% |
| መ. በከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት | 5% |
| ሠ. የማኅበረሰብ | 5% |
| ረ. የሙያ መተዋወቂያ/Induction/ ሥልጠና/ | 5% |
| ሰ. የማህደር ጥራት | 5% |

2.2 ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰልጣኞች/ኢንስትራክተሮች የነጥብ አሰጣጥ

| | |
|---|---|
| ሀ. CGPA | 25% |
| ለ. ለስራ ልምድ/አገልግሎት | 5% |
| ሐ. የስራ አፈጻጸም ውጤት | 25% |
| መ. ኮሚቴ ተሳትፎ | 5% |
| ሠ. ለቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች | 20% |
| ረ. ለኢንደስትሪኤክስቴንሽንስራዎች ... | 15% |
| ሰ. የማህደርጥራት | 5% |

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

2.3 ለ3ኛ ዲግሪ ትምህርት ለሚወዳደሩ የአካዳሚክ ሰራተኞች የማወዳደሪያ መስፈርቶች የነጥብ አሰጣጥ

| | |
|---|---|
| ሀ. CGPA | 10% |
| ለ. አገልግሎት | 5% |
| ሐ. ስራ አፈጻጸም | 20% |
| መ. ኮሚቴ ነክ ጉዳዮች | 10% |
| ሠ. ለጥናትና ምርምር/ቴክኖሎጂ | 25% |
| ረ. የማኅበረሰብ አገልግሎት | 15% |
| ሰ. የማህደርጥራት | 5% |
| ሸ. የከፍተኛዲፕሎማ/ሥልጠና/ | 10% |

ማሳሰቢያ፡- ከCGPA አመዛዘን ስርዓት ውጭ የሆነ የትምህርት ማስረጃ ላላቸው ተወዳዳሪዎች (ለምሳሌ ለቴ/ሙ/ት/ሥልጠና አጠናቃቂዎች) በተቀሩት መስፈርቶች ተወዳድሮ ወደ 100% በመቀየር የሚሰላ ይሆናል፡፡

# አባሪ 3 የነጥብ አሰጣጥ

**ሀ. የትምህርት ዝግጅት (CGPA) ውጤት ነጥብ አሰጣጥ፤**

1/ የCGPA ነጥብ ሲያዝ የተወዳዳሪው ውጤት በግሬድ የተገለጸ ከሆነ 4 ነጥብ ያለው ተወዳዳሪ በአባሪ አንድ ስር የተገለፀውን ነጥብ ያገኛል፡፡ ከ4 ነጥብ በታች ያለው CGPA ወደ መቶኛ እየተሰላ ውጤቱ ይሰጠዋል፡፡

2/ የተወዳዳሪው ውጤት በቁጥር የተገለፀ ከሆነ ከዚህ ቀጥሎ በተገለፀው መሰረት ውጤቱ ወደ CGPA ተቀይሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

A. [85-100].........................A
B. [80- 84) .......................A-
C. [75-79)..........................B+
D. [70-74)..........................B
E. [65-69)..........................B-
F. [60-64)..........................C+
G. [50-59)..........................C

3/ በአባሪ ሶስት ተራ ቁጥር አንድ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተወዳዳሪው በዉጭ ሀገር የተማረ ከሆነና ያስመዘገበው ውጤት በአገሪቱ የአካዳሚክ ፖሊሲ ከተደነገገው አነስተኛ እና ከፍተኛ የመመረቂያ ውጤት የተለየ ቢሆንም በህጋዊ አካል የአቻ ግምት ከተሰጠው ተገቢውን ነጥብ እንዲያመጣ ተቆጥሮ የማወዳደሪያ ውጤቱ ይሰላለታል፡፡

4/ የተወዳዳሪው ውጤት ከ...እስከ በሚል (Range) የተቀመጠ ከሆነ አማካይ ውጤቱ ተወስዶ በአባሪ ሁለት ተራ ቁጥር 1 እና 2 መሰረት ይሰላል፡፡

5/ ለሶስተኛ ዲግሪ ተወዳዳሪዎች CGPA የሚያዘው የሁለተኛ ዲግሪያቸው ውጤት ብቻ ይሆናል፡፡ ሥልጠናው የወሰደው ጊዜ በሰዓት የተቀመጠ ከሆነ በከፍተኛ ትምህርት አካዳሚክ ፖሊሲ ስርዓት ለአንድ "credit hour" የሚመደበው ስዓት ታስቦ የተቀመጠው ጊዜ ወደ "credit hour" ከተቀየረ በኋላ የተቀመጠውን የውጤት ድምር ለ"credit hour" በማካፈል "CGPA"ውን በማስላት ይተገበራል፡፡

**ለ. የስራ ልምድ የነጥብ አያያዝ**

1/ ተወዳዳሪው ከሚሰራበት ተቋም የተገኘ የአንድ አመት አገልግሎት አንድ ነጥብ ያገኛል፤

2/ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን/አሰልጣኞች ከሚሰሩበት ተቋም ውጭ ካሉ አቻ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና/የምርምር ተቋማት የተገኘ አገልግሎትን በተመለከተ፡-

2.1 ከሌላ የግልም ሆነ የመንግስት ወይም አቻ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት/ ተገቢ ከሆነ ኢንደስትሪ ወደሚሠራበት ተቋም በህጋዊ ዝውውር ወይም መልቀቂያ መሠረት በቋሚ ቅጥር ለመጣ የአገልግሎት ነጥብ አያያዝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2.2 ከሌላ ተቋም በዝውውር ወይም በቅጥር የመጣ የአካዳሚክ ሠራተኛ አገልግሎቱ የሚያዘው በቅጥሩ ወይም በዝውውሩ ወቅት ያስያዘው ከሆነ ብቻ ይሆናል፡፡

3/ ተወዳዳሪው አንድ ዓመት የማይሞላ የአገልግሎት ዘመን ያለው ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገውን መሠረት በማድረግ በወራት /በቀናት/ እየተመነዘረ ዋጋ ይሰጠዋል፡፡



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

4/ የከፍተኛ ትምህርት መምህርና ተመራማሪ ከሆነ ለውድድር የሚያዘው አገልግሎት አሁን የያዘውን የትምህርት እርከን ከያዘ ጀምሮ ያለው አገልግሎት ብቻ ነው፡፡

5/ አንድ ተወዳዳሪ በትምህርት የቆየባቸው ዓመታት እንደ አገልግሎት ተቆጥረው ለውድድር አይያዙም፡፡

6/ አምስት አመትና ከዚያ በላይ ያገለገሉ ተወዳዳሪዎች ሙሉ ነጥብ የሚያገኙ ይሆናል፡፡

**ሐ. የስራ አፈጻጸም ውጤት አያያዝ**

1/ አንድ አመልካች ለስኮላርሽፕ ውድድር ሲቀርብ ውድድር ከሚደረግበት ሴሚስተር ጀምሮ ወደኋላ የሁለት ተከታታይ አማካይ የግምገማ ውጤት በአባሪ አንድ አንቀጽ ከ1-3 በተሰጠው ውጤት መሰረት ተሰልቶ ይያዝለታል፡፡

2/ አንድ አመልካች በተለያየ ምክንያት ውድድር ከሚደረግበት ሴሚስተር ጀምሮ ወደኋላ የሁለት ተከታታይ አማካይ የግምገማ ውጤት ከሌለው እና ለስኮላርሽፕ እንዲወዳደር በተቋሙ ከተፈቀደለት በቅርብ ያለው የስራ አፈጻጸም ውጤት ይያዝለታል፡፡

3/ ለስኮላርሽፕ ውድድር የሚቀርብ አመልካች የስራ አፈጻጸም ውጤት የሌለው ከሆነና እንዲወዳደር በልዩ ሁኔታ የተፈቀደለት ከሆነ ለስራ አፈፃፀም ከሚያዘው ነጥብ ዜሮ ይሰጠዋል፡፡

4/ በስራ ባህርያቸው ምክንያት በየስድስት ወሩ የስራ አፈጻጸም ያልተሞላላቸው የተቋማት አመራሮች ለዚህ መስፈርት የተቀመጠውን ውጤት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

**መ. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በልዩ ልዩ ኃላፊነት እና የኮሚቴ ስራዎች ነጥብ አሰጣጥ**

1/ ለኃላፊነት ከተመደበው የነጥብ ድርሻ 60% የሚይዝ ሆኖ በኃላፊነት ተመድቦ ለሰራ የነጥብ አሰጣጡ በመሰረታዊ አመራርነት ለሰራ ለአንድ ዓመት አገልግሎት 1 ነጥብ፣ በመካከለኛ አመራርነት ለሰራ ለአንድ ዓመት አገልግሎት 1.5፣ በከፍተኛ አመራርነት ለሰራ ለአንድ ዓመት አገልግሎት 2 ነጥብ እየታሰበ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

2/ ለኮሚቴ ከተመደበው የነጥብ ድርሻ 40% የሚይዝ ሆኖ በአሰሪው ተቋም ውስጥ በተቋቋሙ የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ተመድቦ ንቁ ተሳትፎ ማድረጉ በሚመለከተው አመራር ሲረጋገጥ በኮሚቴው ለአንድ የአገልግሎት ዘመን/Term/ ያገለገለ ለመስፈርቱ



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

የተቀመጠውን ነጥብ ግማሽ፤ ሁለት ጊዜና በላይ ላገለገለ ለመስፈርቱ የተቀመጠውን ሙሉ ነጥብ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

**ሠ. ለጥናትና ምርምር/ቴክኖሎጂ ሽግግር /ተዛማጅ ስራዎች የነጥብ አሰጣጥ**

በከፍተኛ ተቋማት የደረጃ ዕድገት መመሪያ ዝርዝር መስፈርቶች መሰረት የሚስተናገድ ሲሆን በደረጃ እድገት መመሪያው የማይካተቱ ተቋማት የራሳቸውን ዝርዝር መስፈርት አዘጋጅተው ይተገበራሉ፡፡

**ረ. የማህበረሰብ አገልግሎት / ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን/ ተዛማጅ ሥራዎች ነጥብ አሰጣጥ**

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የደረጃ ዕድገት መመሪያ ዝርዝር መስፈርቶች መሰረት የሚስተናገድ ሲሆን በደረጃ እድገት መመሪያው የማይካተቱ ተቋማት የራሳቸውን ዝርዝር መስፈርት አዘጋጅተው ይተገበራሉ፡፡

**ሰ.የማህደር ጥራት ነጥብ አያያዝ**

ለማህደር ጥራት የነጥብ አሰጣጥ በሲቪል ሰርቪስ መመሪያ መሰረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

**ሸ. የሌሎች ሀገራት የነጥብ አሰጣጥ ተሞክሮ እንደ ምሳሌ**

Converting foreign Countries Cumulative Grade Point Average (CGPA) into Ethiopian grading system of CGPA

$$Ethio_{CGPA} = 4 - \frac{Max_{CGPA} - Actual_{CGPA}}{Max_{CGPA} - Min_{CGPA}}$$

Where,

- $Ethio_{CGPA}$ is CGPA in Ethiopian grading system.
- $Max_{CGPA}$ is the maximum CGPA in foreign country grading system.
- $Min_{CGPA}$ is the minimum CGPA in foreign country grading system.
- $Actual_{CGPA}$ is the actual CGPA the student received in foreign country grading system.

ወይም

ትምህርታቸውን በህንድ አገር ላጠናቀቁ ተማሪዎች

ለምሳሌ፡- ህንድ 10 ነጥብ ከፍተኛው ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ 4 ነጥብ ለመለወጥ አንድ ተማሪ በህንድ 8.44 ቢያመጣ 4.00*8.44/10 = 3.38 ይሆናል ማለት ነው፡፡

ወይም

Example

| | Ethiopia | Germany | Sweden (Lund University) | | |
|---|---|---|---|---|---|
| Max | 4 | 1 | 5 | | |
| | 3.75 | 1.8 | 4 | | |
| | 3.5 | 2.5 | 3 | | |
| | 3.25 | 3.3 | 2 | | |
| Min | 3 | 4 | 1 | | |

## አባሪ 4

### አባሪ 4.1 በተለያዩ አገራት በመንግስትና አጋር አካላት ድጋፍ ስኮላርሽፕ ዕድል ላገኙ ተማሪዎች በመንግስት የሚደረግ ድጋፍ

| ተ.ቁ | ትምሀርቱ የሚሰጥበት አገር | ስኮላርሽፕ የሰጠው አካል | በመንግስት የሚሰጥ የክፍያ ዓይነትና መጠን | | | | | | የትምሀርት ክፍያ | የትራንስፖርት ክፍያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የመኖሪያ አበል | የድጎማ | የምርምር | የመቋቋሚያ | የጤና ኢንሹራንስ በየዓመቱ | ቪዛና ሌሎች ወጪዎች | | |
| 1 | ቻይና | በመንግስት ድጋፍ | $350 | - | $504 | $420 | በስምምነቱ መሰረት | በላኪው ተቋም የሚሸፈን | በስምምነቱ መሰረት | በላኪው ተቋም |
| 2 | ቻይና | በቻይና መንግስት | በቻይና | $75 | የሚወሰን | - | በቻይና መንግስት | በላኪው ተቋም የሚሸፈን | በቻይና መንግስት | በቻይና /በመንግስት |
| 3 | ቻይና | በጋራ ድጋፍ | እስከ $150 | - | $504 | $420 | በቻይና መንግስት | በላኪው ተቋም የሚሸፈን | በጋራ ድጋፍ | በላኪው ተቋም |
| 4 | ህንድ | በመንግስት ድጋፍ | $350 | - | $504 | $420 | በስምምነቱ መሰረት | በላኪው ተቋም የሚሸፈን | በስምምነቱ መሰረት | በላኪው ተቋም |
| 5 | ህንድ | በህንድ መንግስት | በህንድ | $218 | የሚወሰን | በህንድ | በቻይና መንግስት | በላኪው ተቋም የሚሸፈን | በቻይና መንግስት | በህንድ በመንግስት |
| 6 | ቱርክ | በቱርክ መንግስት | በቱርክ | 150/200 EURO | የሚወሰን | በቱርክ | በቱርክ | በላኪው ተቋም የሚሸፈን | በቱርክ | በቱርክ |
| 7 | ቱርክ | በመንግስት ድጋፍ | 560 EURO | 100/125 EURO | $504 | $420 | በስምምነቱ መሰረት | በላኪው ተቋም የሚሸፈን | በስምምነቱ መሰረት | በላኪው ተቋም |
| 8 | ታይዋን | ታይዋን | ታይዋን | - | - | $2000 | በስምምነቱ መሰረት | በላኪው ተቋም የሚሸፈን | በታይዋን | በላኪው ተቋም |
| 9 | ሩሲያ | መንግስት | 410 | | | 250 | 250 | በላኪው ተቋም የሚሸፈን | በሩሲያ | በላኪው ተቋም |
| 10 | ኩባ | ኩባ | | 75 | - | - | ኩባ | በላኪው ተቋም የሚሸፈን | ኩባ | በላኪው ተቋም |
| 11 | ሰርቢያ | ሰርቢያ | | 100 | - | - | ሰርቢያ | በላኪው ተቋም የሚሸፈን | ሰርቢያ | በላኪው ተቋም |
| 12 | ኢራን | መንግስት | 300 | - | በተቋም | - | ኢራን | በላኪው ተቋም የሚሸፈን | በኢራን | በላኪው ተቋም |
| 13 | ጀርመን | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት |
| 14 | ፈረንሳይ | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት |
| 15 | ኮርያ | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት |
| 16 | ደ/አፍሪካ | መንግስት | - | የሀገር ውስጥ ድጋፍ | የሀገር ውስጥ ድጋፍ | - | በስምምነቱ መሰረት | - | በመንግስት | |

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴ... የትምህርት ሚኒ...
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ከላይ በዝርዝር ከተፈቀደው በመንግስት የበጀት ድጋፍ በውጭ ሀገር እና በሀገር ውስጥ ለሚሰጡ ሥልጠናዎች ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ቀርቦ በቀን 21/05/04 ቁጥር መ190-1013/1 በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በተወሰነው መሰረት፡

1/ ለትምህርት ክፍያ (Tution Fees) በዓመት በአማካይ $5,000 (አምስት ሺህ የአሜሪካን ዶላር) የጊዜ ቆይታ ለ3ኛ ዲግሪ እስከ 4 ዓመትና ለ2ኛ ዲግሪ 2 ዓመት ይሆናል፡፡

2/ ለትራንስፖርት ክፍያ በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ ለሁለተኛ ዲግሪ የአንድ ጊዜ ደርሶ መልስ የአውሮፕላን ትኬት እና ለ3ኛ ዲግሪ የሁለት ጊዜ ደርሶ መልስ የአውሮፕላን ትኬት ይሆናል፡፡

3/ ለመኖሪያና ለመሳሰሉት በወር $350 በተፈቀደው መሰረት ድጋፍ ይደረጋል፡፡

**አባሪ 4.2 በሀገር ውስጥ ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ የሚሰጥ ጥቅማ ጥቅምና አገልግሎት**

ምንም እንኳ በተመራማሪ ተማሪዎች በድጋፉ ማነስ ቅሬታ እየቀረበ ቢሆንም በመንግስት የበጀት ድጋፍ በሀገር ውስጥ ለሚሰጠው ስኮላርሽፕ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ቀርቦ በቀን 21/05/04 ቁጥር መ190-1013/1 በጽ/ቤቱ በተፈቀደው መሰረት መንግስት የሚከተሉትን ድጋፎች ያደርጋል፣

1/ በሚደረግ የግዴታ ውል ስምምነት መሰረት ትምህርት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ይሸፈናል፤

2/ የቤት ኪራይ ድጋፍ በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ በየወሩ ለአዲስ አበባ 1,000 (አንድ ሺህ ብር) እና ከአዲስ አበባ ውጪ 700 (ሰባት መቶ ብር) ይሆናል፣

3/ የትራንፖርት ድጋፍ በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ በየወሩ ለአዲስ አበባ 250 (ሁለት መቶ ሀምሳብር) እና ከአዲስ አበባ ውጪ 150 (አንድ መቶ ሀምሳ ብር)፣

4/ ለጽህፈት፣ ለጽህፈት መሳሪያ ግዥና የፎቶ ኮፒ አገልግሎት ድጋፍ በላኪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ በአዲስ አበባና ሌሎች ቦታዎች በተመሳሳይ በየወሩ 500 (አምስት መቶ ብር) ድጋፍ ያደርጋል፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

5/ የጥናትና ምርምር ድጋፍ በአስተማሪው ተቋም የሚሸፈን ሆኖ፡-

- ለሶስተኛ ዲግሪ ተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ 60,000 (ስድሳ ሺ.ህ ብር)
- ለሶስተኛ ዲግሪ ለማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ 45,000 (አርባ አምስት ሺ.ህ ብር)
- ለሁለተኛ ዲግሪ ለተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ 25,000 (ሀያ አምስት ሺ.ህ ብር)
- ለሁለተኛ ዲግሪ ማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ 15,000 (አስራ አምስት ሺ.ህ ብር) ለአንድ ጊዜ ብቻ ድጋፍ ያደርጋል፡፡